بسم الله الرحمن الرحيم

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት

المجلس العالي للشؤن الاسلامية في مدينة اديس ابابا

ISLAMIC AFFAIRS SUPREME COUNCIL OF ADDIS ABABA

---

ቁጥር እአእጉ/ 0547 /98 ........................ رقم

ቀን ነሐሴ 11/98 ........................ التاريخ

ለሁሉም መስጊዶች በሙሉ
<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ፡- በአራት <u>ኪሎ መስጊድ ጉዳይ በተመለከተ</u>**

በአራት ኪሎ አካባቢ በተፈጠረ ሁኔታ ም/ቤቱ ለመንግስት በአቀረበው ጥያቄ መሠረት ቦታ የተሰጠ መሆኑን ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ የተላከው መግለጫ የሚያስረዳ ስለሆነ ይህንን መሠረት በማድረግ ስለ ሰላም ጠቃሚነት ከአስር ሰዓት ጀምሮ ለሕዝቡ እንዲገለጽ በአላህ ስም እንጠይቃለን።

አላሁ አክበር

ሐጂ መሐመድ አወል ነጋ ገላ
ዋና ፀሐፊ
الحاج محمد أول نغا غلا
السكرتير العام للمجلس
Haj Mohammed Awall Naga Gala
General Secretary

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው
ከአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
ለመላው ሙስሊም ኅብረተሰብ የተሰጠ መግለጫ

በአራት ኪሎ አካባቢ ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ የመስገጃ ቦታ እንዲሰጥ ከመንግስት በተጠየቀው መሠረት 10/12/98 ቦታውን በመመልከት የተረከብን ሲሆን ቦታውም ከአፍንጮ በር ወደ ስድስት ኪሎ የሚወስደው መንገድ በስተቀኝ ወደ ራስ መኮንን መታጠፊያ መንገድ ጠርዝ ላይ ስፋቱ 2230 ካሬ ሜትር ቦታ መሆኑ ተረጋግጧል።

ይህ ቦታ በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሚማሩ ሙስሊም ተማሪዎች አመቺ ከመሆኑ በተጨማሪ በዋናው መንገድ ላይ የተሰጠን በመሆኑ የተሰጠንን በማልማትና መስጊዱን በመገንባት ተግባር ሁሉም የከተማው ሙስሊም ባለሃብትና ኅብረተሰቡ እንዲረባረብ እንጠይቃለን።

በመጨረሻም መንግስት በአፋጣኝ ለሰጠው በጎ ምላሽ ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ በህገ መንግስቱ የተሰጠውን መብት የማስከበር ተግባር በአግባቡ የተወጣ ስለሆነ በከተማው ሙስሊም ኅብረተሰብ ስም እያመሰገንን ከዚህ ውጭ በተሳሳተ መረጃ ወይም ሌላ ፍላጎት ባላቸው አካላት በመነሳሳት ነሃሴ 5/98 በታላቁ አንዋር መስጊድና በአራት ኪሎ አካባቢ የተፈጠረውን አይነት ሁከትና ብጥብጥ ተግባር የሙስሊሙን መብት ማስከበር ሳይሆን የሙስሊሙን መብት የሚጎዳ ስለሆነ ወደፊትም ቢሆን ማንኛውም የከተማው ሙስሊም ከዚህ ተግባር እንዲጠበቅ እውነታውንና ሃቁን ከም/ቤቱ በማንኛውም ጊዜ ቀርቦ መረዳት የሚችል መሆኑን እንገልፃለን።

አዲስ አበባ
ነሃሴ 11/1998